Click Here & Upgrade
Expanded Features
Unlimited Pages
PDF Complete

የኢትዮጵያ ሚሌኒየም ፪ሺ
ETHIOPIAN MILLENNIUM 2000

# የኢትዮጵያ ሚሌኒየም በዓል አከባበር ምክር ቤት ጽ/ቤት መሪ ቃል፣ ራዕይና ተልዕኮ እንዲሁም የፕ/ት ግርማና የጠ/ሚ/ር መለስ መልዕክቶች

## መሪ ቃል

በአንድነትና በሕብረት ወደ በለፀገች ኢትዮጵያ!!

## ራዕይ፡-

‘‘ኢትዮጵያዊያንና የኢትዮጵያ ወዳጆች እጅ ለእጅ ተያይዘው በጋራ ስሜት የሚያከብሩትን የሚሌኒየም በዓል በማስተባበር የአገራችንን ገፅታ በመለወጥ የመጀመሪያ የሰው ልጅ መገኛ መሆኗን ዳግሞ በማረጋገጥ ከሁሉ በሁሉ ተመራጭ ሀገር ሆና ማየት ነው፡፡’’

## ተልዕኮ

“በመላው የኢትዮጵያ ሕዝቦች ወዳጆቻቸው የሚሳተፉበት ይህን ታሪካዊና በዓይነቱ የተለየ የሚሌኒየም በዓል እጅግ ደማቅ በሆነ መንገድ በማዘጋጀት ባለብዙ ዘርፍ እንቅስቃሴ በማካሄድ ብሔራዊ ገጽታችን በማደስ በጋራ አገራዊ አመለካከትና ራዕይ ለዘላቂ ልማትና ለመልካም አስተዳደር ግንባታ በቆራጥነት መነሳሳታችንን ማስመስከር፡፡’’

Click Here & Upgrade
Expanded Features
Unlimited Pages
PDF Complete

“ … የልጅነት ትዝታዬን ላውጋችሁ በእረኝነት ጊዜዬ ጠዋት ከቤት ወጥተን ማታ ወደ ቤት እንስክንመለስ ድረስ የምንመገበው ደን ያፈራውን ፍራፍሬ ነበር። አጋሙ፣ ቀጋው፣ ሾላውና ኮሽም የማይገኙበት አካባቢ ስለሌላ ስንበላ ውለን ማታ ቂጣና ወተት አከለንበት እንተኛለን። የደን ስፋትና ብዛት ምን ያህል እንደነበረ ለመግለፅ ነው።

ከእረኛኛነት ጊዜዬ በሀላ ከዛሬ ስድሳ ዓመታት በፊት የበረራ ተማሪ ሆኜ የአገር ማቋረጥና ቦታ የመለየት ትምህርት ስንማር የሀገሬን መልክዓምድራዊ አቀማመጥና የደን ሀብቷን የማየት ዕድል ነበረኝ ድንገት ሞተር ቢበላሽ የት እናርፋለን በማለት ከመፍራት ውጭ ልቤ በኩራት የተሞላ ነበር። ዛሬም በሥራ አጋጣሚ ወደተለያዩ የሀገራችን ክፍሎች ስጓዝ የሀገሬን መልክዓምድራዊ አቀማመጥ አያለሁ፤ የደን ሀብቷ ተራቁቶ ሳይ አዝናለሁ።…… የዚህ ውጤት ለሀገራችን ገፅታ መበላሸት ዋነኛ ምክንያት ሆኖ ድርቅ ረሀብ መለያችን እንዲሆን፤ በመልካም ገጽታችን ላይ ጥላሸት እንዲያጠላበት አድርጎታል። ለደን ሀብታቸን መመናመንና ከዚሁ ጋር ተያይዘው ለተፈጠሩተ ቸግሮች ተጠያቂዎቹ እኛው ነን። ችግሩን ለማስወገድም መፍትሄው እኛው እጅ ያለና በራሳችን ሊከናወን የሚችል ነው ይህንን ማድረግ ደግሞ ለነገ የሚባለ አይደለም፤ ለመጭው አዲስ ሚሊኒየም መልካም እሴቶቻችንን ጠብቀንና የልማት ጅማሮውን ተልመን የማሸጋገሩ ሀላፊነቱ ያረፈው በእኛ ላይ ነው።”

ክቡር አቶ ግርማ ወልደጊዮርጊስ
የኢፌዲሪ ፕሬዚዳንት
ሚያዚያ 18 ቀን 1999 ዓ.ም

“… አዲሱ ሦስተኛው ሺህ ዓመት ካለፈው ሺህ ዓመት በእጅጉ የተለየ መሆን ይኖርበታል። አዲሱ ሚሌኒየም የኢትዮጵያ ብልፅግና ሚሌኒየም ሊሆን ይገባል። ልማታችን ተፈጥሮና ያለማቋረጥ ተከናውኖ የኢትዮጵያ ሕዝቦች ተመልሰው የዓለም የስልጣኔ የመጀመሪያው ጠርዝ ላይ የሚደርሱበት ዘመን ሊሆን ይገባል። አዲሱ የኢትዮጵያ ሚሌኒየም በአገራችን ዲሞክራሲና መልካም አስተዳደር የሚሰፍንበት ዘመን ሊሆን ይገባል። ዘላቂና አስተማማኝ ሰላም የሚሰፍንበት፣ ከጎረቤቶቻችን ጋርና ከመላው የዓለም ሕዝብ ጋር በጋራ ጥቅም ዙሪያ በሰላምና በመቻቻል የምንኖርበት ዘመን ሊሆን ይገባል። በአጭሩ አዲሱ ሚሌኒየም የልማት የሰላምና ዲሞክራሲ ዘመን ሊሆን ይገባል።”

ክቡር አቶ መለስ ዜናዊ
የኢፌዲሪ ጠቅላይ ሚኒስትር
ታህሳስ 4/1999 ዓ.ም